

# 22ኛው ዓለም ዓቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን

## አዲስ አበባ በፀረ - ሙስና ትግሉ

አዲስ አበባ ፈጣን የከተማ ዕድገት በማስመዝገብ ኢኮኖሚያዊ አቅሟን እና ማህበራዊ ከባቢዋን ተዓምር በሚመስል መልኩ እየቀየረች ያለች ተምሳሌታዊ ከተማ ናት፡፡ ባለፉት ዓመታት በፀረ-ሙስና ትግሉ በተሰሩ አመርቂ ስራዎች ሊመዘበሩ የነበሩ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማዳን በከተማዋ በአጭር ጊዜያት ፈጣን ልማቶችን ማስመዝገብ የቻለች ሲሆን በተለይም በመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ በቴክኖሎጂና በአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያዎች አስደናቂ እምርታን አሳይታለች፡፡

ከተማ አስተዳደሩ ሙስና ለከተማዋ ልማትና መልካም አስተዳደር እንቅፋት እንዳይሆን ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በልዩ ትኩረት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንን በአዋጅ ቁጥር 75/2014 በማቋቋም በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ቁርጠኛ መሆኑን አሳይቷል፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

በከተማ አስተዳደሩ በተቋቋመው የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ረገድ ካለፉት ሶስት ዓመታት ጀምሮ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡

**ሙስና ስጋት የማይሆንባት አዲስ አበባን እንፈጥራለን!**

# በኮሚሽኑ ከተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት መካከል፡-

👉 **ለ3,727,911** የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርቷል።

👉 **ለ713,850** አመራርና ሰራተኞች በተለያየ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ስልጠና መስጠት ተችሏል።

👉**114,079** አመራሮች፣ ዳይሬክተሮች፣ ቡድን መሪዎችና ሰራተኞች ሃብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተደርጓል።

👉**380** ጥናቶችን በማጥናት የተቋማት አሰራር ስርዓት የሙስና ተጋላጭነታቸውን የመለየት፣ ምክረ ሀሳብ የመስጠትና የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ መደረጋቸውን የመከታተል ስራ ተሰርቷል።

👉በአስቸኳይ እና መደበኛ ሙስና መከላከል ስራ ከ**10.4** ቢሊየን ብር በላይ እና **57,452.32 ካሬ ሜትር** መሬት የህዝብና የመንግስት ሀብት የማዳን ስራ ተሰርቷል።

👉በብልሹ አሰራር ውስጥ ገብተው የተገኙ **12,062** አመራር፣ ፈጻሚና ደላላ ከቀላል ዲሲፒሊን እስከ ፍርድ ቤት በወንጀል ተጠያቂ ሆነዋል።

**በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን**
**ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ**
**ህዳር 2018 ዓ.ም**

**ለጥቆማ**
☎ 8887